ተአምራዊው የኢስራና ሚዕራጅ ጉዞ

ትውስታዎቹና አስተምህሮቱ

- የረጅብ ወር ሲመጣ አንድ ታላቅ ክስተት ሁሌም አዕምሮችንን ላይ ያቃጭላል) መላ ሀልውናችንን ይቆጣጠራል፤ በትዝታ አለም አስምጦን የሩቁን ዓለም ከተጨባጯችን ጋር ለማስተሳሰር ይገፋፋናል። በሀያ ሰባተኛው ሌሊት የተከሰተው ታላቁና ተአምረኛው ጉዞ! የኢስራዕ ሚዕራጅ ተአምራዊ ጉዞዎች የነብዩ ሙሐመድን (ሶ.ዐ.ወ) ና የተቀሩት ነብያትን ታላቅነትና ክብር ሊያስተምሩን ተከሰቱ።

-ጉዞው የዚህ ኡመት(ሕዝብ) ታላቅነት ካለፉት በላይ እንደሆነ የሚጠቁሙ ትዕይንቶችንም አስተናግዷል። ምክንያቱም የክስተቱ ዋና ተዋናይ የዚህ ሕዝብ መሪ ነብዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ናቸው:: ብጉዞው የአላህን ታላላቅ ተዐምራት በዓይናቸው ተመልከተውበታል:: ከርሳቸጡ ውጭ የሆኑ ነብያት ያላዩዋቸውን ታላላቅ ነገሮች አይተዋል:: ታላቁ

የኢስላም ምሶሶ ሶላት የተደነገገው በዚህ ገዞ ውስጥ ነው:: አላህ እንዲህ አለ።

سبحان الذي أسرى بعبده ليلا من المسجد الحرام إلى المسجد الأقصى الذي باركنا حوله لنريه من آياتنا إنه هو السميع الصبر [١٧:١]

'ያ ባርያውን ከተኣበረው መስጂድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኼደው ጌታ ጥራት ይገባው፡- ከተና ራቶቻችን ልናሳየው (አስኼድነው)። እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚው ተመልካቸው ነው:: (አል- ኢስራእ(17)-1)

አላህ ታላቁን መልት ነውን..ር.ወ) ከተከበረው መስጂድ -ከመካ ወደ መስጂዱል አቐሷ (ፍልስጤም) በለሊት እንዲጓዙ አድርጓ የጉዟቸው ሂደትም ሁለት ክስተቶችን አስተናግዷል:: ኢስራእ ከዚያም ሚዕራጅ::

ኢስራእ ምንድን ነው? ሚዕራጅስ?

በዓረብኛ ቋንቋ ትርጉሙ ኢስራእ ማለት ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ በለሊት የሚደረግ ጉዞ ነው:: በያዝነው ነብያዊ ታሪክ ውስጥ ደግሞ ታላቁ ተዓምርን ይጠቁማል። እርሱም ነብዩ ሙሐመድ(ሶ.ዐ.ወ) ከመስጂዱል ሐረም (መካ ከሚገኘው የተከበረ መስጂድ) ወደ መስጂዱል አቐሷ (ኢየሩሳሌም) በአንድ ለሊት ያደረጉት ጉዞ ነው።

ሚዕራጅ ማለት ደግሞ ወደላይ መውጣት /መጠጣ ማለት ሲሆን እዚህ ላይ ግን ለመጥቀስ የሚሞከረው ነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) ከመስጂዱል አቐሷ ወደ ሰማይ ያደረጉት ጉዞ ነው:: ሁለቱም ክስተቶች በተከታታይ ስለተከሰቱ በአንድነት የኢስራ እና ሚዕራጅ ጉዞ እያልን እንጠራቸዋለን።

ልብ እንበል ኢስራእ ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም በለሊት የተካሄደ ጉዞ ሲሆን ሚዕራጅ ደግሞ ኢስራእ በተከሰተበት ለሊት ከኢስራእ ቀጥሎ ከኢየሩሳሌም ወደ ሰባት ሰማያት የተደረገ ጉዞ ነው:: ሁለቱም ነብያዊ ተዓምራት ናቸው::

የኢስራእ ክስተት በይፋ በቁርአን ውስጥ የተዘገበ በመሆነ ዑለሞች- ክስተቱን ያስተባበለ ከእስልምና ይወጣል ይላሉ:: ሚዕራጅ ደግዛ የተዋቱር ደረጃ ባልደረሱ የሀዲስ ዘገባዎች የተዘገበና በሱረቱ እን-ነጅም ውስጥ አሻሚ በሆነ ሁኔታ የተጠቀሰ በመሆኑ እርሱን ያስተባበለ ፋሲቅ (አመፀኛ) ይሆናል እንጂ ከእስልምና አይወጣም ይላሉ- ዑለሞች።

የኢስራእና ሚዕራጅ ክስተት መች ተከሰተ?

ብዙ ዑለሞች ኢስራእና ሚዕራጅ የተከሰተው ከሂጅራ በፊት አምስተኛው አመት ላይ እንደሆነ ያምናሉ:: መላኢካው ጂብሪል (ዐ.ስ) እርሳቸው (ሲ.ዐ.ወ) እንቅልፍ ውስጥ በነበሩበት ለሊት መጣ:: መልእክተኛው (ሲ.ዐ.ወ) የአጎታቸው ልጅ -ኡሙ ሀኒእ ቤት ውስጥ ነበር የተኙት: ከእንቅልፍ ቀሰቀሳቸውና ቡራቅ የተሰኘው የነብያት መጓጓዣ ላይ ጫናቸው። ከዚያም ጉዞው ተጀመረ።

አማም ሙስሊም በሶሂህ ኪታባቸው ውስጥ እነስ ኢብኑ ማሊክን (ረ.ዐ) ዋቢ በማድረግ እንደጠቀሱት የአላህ መልእክተኛ (ሊ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- - ቡራቅ መጣልኝ:: (አርሱ ነጭ መጓጓዣ ነው። ከአህያ ከፍ ይላል። ከበቅሎ ያንሳል - ዓይነ የሚያየው ድረስ በአንዴ መርገጥ ይችላል። ከዚያም ጋለብኩት:: በይቱል መቅዲስ (አልአቅሷ መስጂድ) ደረስኩኝ። ከዚያም ነቢያት

መጓዛቸውን የሚያስሩበት ቦታ ላይ አስርኩት። ወደ መስጂዱ ገባሁና ሁለት ረከዓዎችን ስገድኩ:: ከዚያም ጅብሪል (ወስ) ኽምር (አልክሆል) ያለበትና ውተት ያለበትን እቃ አመጣና ምረጥ አለኝ። እኔም ወተቱን መረጥኩኝ። እርሱም ተፈጥሮን መርጠሀል። ኽምርን ብትመርጥ ህዝቦችህ ይጠሙ ነበር አለኝ...″

አንዳንድ የጉዞው ክስተቶች

1. የደረት መስንጠቅ

ቡኻሪይ ከማሊክ ቢን ስዕስዓህ እንደዘገቡት የአላህ ነብይ (ሲ.ወ) ወደ ኢየሩሳሌም ስለተደረገላቸው ጉዞ ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል- እኔ ካዕባ (የአላህ ቤት) አካባቢ ተኝቼ (ተንጋልዬ) ሳለሁ የሚመጣነገር መጣኝ። እንዲህ ሲሉም ሰማሁ ከዚህ እስከዚህ ሰነጡኝ አጠገቤ ጃሩድ ነበርና ምን ማለት ነው ብዬ ጠየቅኩት ከአንገታቸው ጉድጓድ እስከ እምብርታቸው ማለታቸው ነበር።" አለኝ:: ከዚያም እንዲህ አሉ "ልቤን አወጣውና አወርት የሆነ ኢማን የተሞላ- ድስጥ አምጥቶ ልቤን አጠው:: ከዚያም ሞላውና መለሰው..

2 በይቱል መቅዲስ (የፍልስጤም ቤተ መቅደስ)

ነሳኢይ በሰነዳቸው ከአነስ ቢን ማሊክ (ረ.ዐ) ይዘው እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፦ - hile me በይቱል መቅዲስ (የአልአትሳ መስጊድ ዛሁ። ካብዖት አላህ ሰላም ይድረሳቸውና ተሰበሰቡልኝ። እኔን ጂብሪል (ዐ.ሰ) አስቀደመኝና አስገድኳቸው::

3. ቅርቧ ሰማይ (ሰማኡ ዱንያ) ውስጥ

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ - ጂብሪል (ዐስ) ይዞኝ ሄደ። ቅርቧ ሰማይ ጋር ስንደርስ እርሱ ላስፈቀደ። ማነህ?' ተባለ:: ጂብሪል ነኝ አለ። አብሮህ ማን አለ? ሲሉት ሙሐመድ አለ:: ተልኮቡት ነው የመጣው? አለት። "አዎን!' አለ። እንኳን ደህና መጣ:: ይግዛ:: ጥሩ አመጣጥ አጥቷል:: አሉኝና ወደውስጥ ስገባ እዚያ ሰማይ ውስጥ (አባታችን) አደምን (ሰ.ዐ.ወ) አገኘሁት። ጅብሪል (ዐ.ሰ) ይህ አባትህ አደም ነው። ሰላምታ ስጠው' አለኝ፡ እኔም ሰላም አልኩት:: ሰላምታዬን መለሰልኝ። ከዚያም መልካሙ ልጄ ደጉ ነብይ ሆይ አንኳን ደህና መጣህ! አለኝ"

በሌላ ሰነድ እንደተዘገበው መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፦ ጉጂብሪል) እዴን በመያዘ ወደ ሰማይ ይዞኝ ወጣ። ወደ ቅርቢቱ ሰማይ ስመጣ ጂብሪል (ዐ.ሰ) የሰማይን ዘበኛ ክፈት አለው:: እሱም ማነው?" አለ:: ጅበሪል ነኝ አለ አብሮህ ሌላ አለ?' ተባለ:: 'አዎን! ሙሐመድ አለ' አለ:: ተልኮበት ነው የመጣው? አለ:: አምን? እለ፣ ጂብራል ሲከፍትልን ወደ ላይ ዘለቅን:: እዚያም አንድ ሰው ተቀምጦ አየሁ:: በቀኙ በኩል ብዙ ጭፍራዎች አሉ : በግራውም በኩል እንዲሁ ወደ ቀኞቹ ሲመለከት ይስቃል:: ወደ ግራው ሲመለከት ያለቅሳል:: ከዚያም እኔን ሲመለከት ደጉ ነብይ መልካሙ ልጄ እንኳን ደህና መጣህ አለኝ። እኔም ጂብሪልን 'ይህ ሠው ማን ነው? አልኩት:: 'ይህ ዐደም (ዐሰ) ነው። በቀኝና በግራ በኩል ያሉት ህዝቦች የልጆቹ ሩሆች ናቸው። በግራ በኩል ያሉት የአሳት ናቸው:: ለዚህ ነው ወደ ቀን ሲመለከት የሚስቀውና ወደ ግራ ሲመለከት የሚያለቅሰው አለኝ::"

4. ሁለተኛው ሰማይ ውስጥ

ከዚያም ይዞኝ ወጣ:: ሁለተኛው ሰማይ ላይ ስንደርስ እንዲከፈትለት አስፈቀደ። ማነው ተባለ:: ጂብሪል ነኝ። አለ አብሮህ ማን አለ? ተባለ። 'ሙሐመድ አለ: ተልኮበት ነው የመጣጡን' ተባለ። 'እዎን አለ፣ ጂብሪል (ዐሰ) እንኳን ደህና መጣ ይግባ!' ተባለና ተከፈተልን። ወደ ውስጥ ስገባ ነቢዩ የሀያ (ዐ.ሰ) እና ዒሳን (ዐሰ) አገኘኋቸው እነርሱ የአክስት ልጆች ናቸው:: ጂብሪልም ይህ የሀያ ነው፡ ይህ ደግሞ ዒሳ ነው። ሰላም በላቸው:: አለኝ: እያንዳንዳቸውን በግል ሰላም አልካቸው:: ከዚያም መልካሙ ወንድማችን ደጉ ነብይ እንኳን ደህና መጣህ? አሉኝ...

5 ሦስተኛው ሰማይ ላይ

ከዚያም ወደ ሦስተኛው ሰማይ ይዞኝ ወጣ እና እንዲከፈትለት አስፈቀደ:: ማንሱት አሎት: ጂብሪል ነኝ አለ። አብሮህ ማን አለ? አሉት። ሙሐመድ አለ:: ተልኮበት ነው የመጣሁ? አሉ:: አዎን!" አለ። እንኳን ደህና መጣ አሉኝ″...

ጥሩ አመጣጥም መጥታል አሉ። ወደ ውስጥ ስንገባ ነቢዩ ዩሱፍን (ዐ.ሰ) አገኘነው። 'ይህ ዩሱፍ ነው:: ሰላም በለው:: አለኝ። ሰላም አልኩት:: እርሱም ሰላምታዬን ከመለሰ በኋላ መልካሙ ወንድሜ ደጉ ነብይ! እንኳን ደህና መጣህ!' አለኝ።...

6. አራተኛው ሰማይ ላይ

ከዚያም ወደ አራተኛው ሰማይ ይዞኝ ወጣ:: እና አንዲከፈትለት አስፈቀደ:: ማነው!' አሉት። ጂብሪል ነኝ አለ። አብሮህ ማን አለ? አሉት። 'ሙሐመድ' አለ። ተልኮበት ነው የመጣው? አሉ:: 'አዎን!' አለ። 'እንኳን ደህና መጣ ጥሩ አመጣጥም መጥቷል::' አሉ። ወደ ውስጥ ስንገባ ነቢዩ ኢድሪስን (ዐ.ስ) አገኘነው። 'ይህ ኢድሪስ ነው:: ሰላም በለው:: ' አለኝ፡ ሰላም አልኩት። እርሱም ሰላምታዬን ከመለሰ በኋላ መልካሙ ወንድሜ ደጉ ነብይ! እንኳን ደሆና መጣህ!' አለኝ::"....

7. አምስተኛው ሰማይ ላይ

ከዚያም ወደ አምስተኛው ሰማይ ይዞኝ ወጣና እንዲከፈትለት አስፈቀደ። ማነው!' አሉት። 'ጂብሪል ነኝ አለ። አብሮህ ማን አለ?' አሉት:: 'ሙሐመድ' አለ። ተልኮበት ነው የመጣው?' አሉ። 'እምን!' አለ። 'እንኳን ደህና መጣህ ጥሩ አመጣጥም መጥቷል።' አሉ። ወደ ውስጥ ስንገባ ነቢዩ ሀሩንን (ዐ.ስ) አገኘነው:: 'ይህ ሀሩን ነው:: ሰላም በለው:: አለኝ: ሰላም አልኩት። እርሱም ሰላምታዬን ከመለስ በኋላ 'መልካሙ ወንድሜ ደጉ ነብይ! እንኳን ደህና መጣህ!' አለኝ::"...

8. ስድስተኛው ሰማይ ላይ

ከዚያም ወደ ስድስተኛው ሰማይ ይዞኝ ወጣ እና አንዲከፈትለት አስፈቀደ። ማነው!' አሉት:: ጂብሪል ነኝ አለ። አብሮ'ህ ማን አለ?' አሉት:: 'ሙሐመድ' አለ:: 'ተልኮበት ነው የመጣው?' አሉ። 'እምን!' አለ። እንኳን ደህና ጥሩ አመጣጥም መጥቷል።' አሉ። ወደ ውስጥ ስንገባ ሙሳን አገኘነው። 'ይህ ሙሳ ነው:: ሰላም በለው:: አለኝ። ሰላም አልኩት። እርሱም ሰላምታዬን ከመለስ በኋላ መልካሙ ወንድሜ ደጉ ነብይ! እንኳን ደህና መጣህ!' አለኝ። ከዚያም አልፈ፤ው ልሄድ ስል አለቀሰ:: 'ምን ያስለቅስኻል?' ተባለ። እርሱም ከእኔ በኋላ ከተላከው ወጣት ህዝቦች ከኔ ህዝቦች ቁጥር በላይ ወደ ጀነት ይገባል፤ ለዚያ ነው የማለቅሰው። አለ።*...

ከዓብዱላህ ኢብኑ ዓባስ (ረ.ዐ) እንደተዘገበው፡- መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ኢስራእ ባደረጉበት ጊዜ የሆነውን ሲገልፁ እንዲህ ብለዋል- ንብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ጠይምና ረዥም ነው:: ልክ የሸኑእ ጎሳ ሰዎችን ይመስላል: ዒሳ (ዐ.ሰ) ደግሞ ፀጉሩ ዞማና መሀከለኛ ቁመት አለው::"

9. ሰባተኛው ሰማይ ላይ

ከዚያም ወደ ሰባተኛው ሰማይ ይዞኝ ወጣ:: እና እንዲከፈትለት አስፈቀደ። ማነው!' አሉት። ጂብሪል ነፃ አለ:: አብሮ'ህ ማን አለ?' አሉት:: 'ሙሐመድ አለ። ተልኮበት ነው የመጣው? አሉ። አዎን!' አለ። እንኳን ደህና መጣ ጥሩ አመጣጥም መጥቷል::' አሉ። ወደ ውስጥ ስንገባ ነብዩ ኢብራሃምን አገኘነው:: 'ይህ አባትህ ነው :: ሰላም በለው። አለኝ። ሰላም አልኩት:: እርሱም ሰላምታዬን homen በኋላ 'መልካሙ ልጅ ደጉ ነብይ! አንኳን ደህና መጣህ!

ሙስሊም ከአነስ ቢን ማሊክ (ረ.ዐ) ይዘው በዘገቡት መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ:- ገዚያም ወደ ሰባተኛው

ሰማይ ይዞኝ ወጣ እና እንዲከፈትለት አስፈቀደ። ማነው!' አሉት:: ጂብሪል ነኝ አለ:: 'አብሮህ ማን አለ? አሱት።

ሙሐመድ' አለ። ተልኮበት ነው የመጣው?" አሉ:: አሥን!' አለ። እንኳን ደህና መጣህ ጥሩ አመጣጥም መጥቷል።

አሉ:: ወደ ውስጥ ስንገባ ኢብራሃምን (ሰ.ዐ.ወ.) በጀርባው በይቱል መዕሙርን ተደግፎ አገኘነው :: በይቱል መሙ

(ልክ ሠዎች በምድር ውስጥ በካዕባ ዙሪያ እንደሚዞሩና አምልኮ እንደሚፈፅሙ በሰባተኛው ሰማይ ውስጥ የሚኖሩ

መልአኮች የሚዞሩትና አምልኮ የሚፈፅሙበት ቤት ነው::) በየቀኑ ሰባ ሺህ መላኢካዎች ይገቡብታል:: ከዚያም አይደግሙትም።

10. ሱድረቱል ሙንተሀ (የእውቀት መድረሻይቱ ቁርቁራ)

ከዚያም ሲድረቱል ሙንተሀ ተገለጠችልኝ። ፍሬዎቿ የሀጀር እንስራ ያህላሉ። ቅጠሎቿ ደግሞ የዝሆን ጆሮ ያህላሉ። 'ይህች

ሲድረቱል ሙንተሀ ናት አለኝ፡ ጂብሪል። እዚያው አራት ወንዞችን ተመለከትኩ። ሁከቱ ወደ ውስጥ ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ወደ ውጭ ናቸው። እንዚህ ማን ይሆን ብዬ ጂብሪልን ጠየቅኩት። እርሱም እነዚህ ወደ
ውስጥ የሆኑት ጀነት ውስጥ ያሉ ሁለት ወንዞች ናቸው:: እነዚህ ወደ ውጭ የሆኑት ደግሞ ናይልና ፉራት (ኢፍራተስ) ናቸው።

በሌላ ዘገባ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- "ሲድረቱል ሙንተሀ እስክንደርስ ይዞኝ ተጓዘ። እርሷንም ምን እንደሆነ የማላውቃቸው የተለያዩ ፍሬዎች ሸፍነዋታል:: ከዚያም ወደ ጀነት ገባሁ:: በውስጧም ከሉል የሆኑ ዳገቶችን አገኘሁ። አፈሯም ከሚስክ ነው::...

በሌላ ዘገባ እንዲህ የሚል ተገኝቷል- ከዚያም ወደ ሲድረቱል ሙንተሀ ይዞኝ ሄደ:: ቅጠሎቿ የዝሆን ጆሮ ያህላሉ። ፍሬዎቿ ደግሞ እንስራ ያህላሉ:: ከአላህ ትእዛዞች የሚሸፍን የሆነው በሚሸፍናት ጊዜ ትለወጣለች:: ከውበቷ ማራኪነትም ማንም ሊገልፃት አይቻለውም:: ከዚያም አላህ ሊያወርድ የሻውን ራእይ በኔ ላይ አወረደ::...

11. የሶላት መደንገግ

ከዚያም በየቀኑ የሚሰገዱ ሀምሳ ሶላቶች ግዴታ ሆኑ:: እነርሱን ይዤ ተመለስኩኝ። በነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) በኩል ላልፍ 'በምን ታዘዝክ?' አለኝ:: ሀምሳ ሶላቶችን ታዘዝኩኝ አልኩት:: እርሱም ህዝቦችህ ሀምሳ ሶላቶችን አይችሉም:: እኔ ወሏሂ ካንተ በፊት ሥዎችን ሞክሬያቸኋለሁ:: የእስራኤል ልጆችን ብርቱ ትግል ታግያቸኋለሁ:: ወደ ጌታህ ተመለስና እንዲቀንስልህ ለምነው::' አለኝ። እኔም ተመለስኩና አስር ተቀነሰልኝ:: ከዚያም በነብዩ ሙሳ በኩል ላልፍ መጀመሪያ የጠየቀኝን ጥያቄ ጠየቀ:: መልሴን ከሰማም በኋላ እንዳስቀንስ ነገረኝ። ከዚያም በድጋሚ ተመልሼ ጌታዬ እንዲቀንስልኝ ተማፀንኩት። አስር ተቀንሶልኝ ስመለስ አሁንም ሙሳ ተመሳሳይ ነገር አሉኝ። ከዚያም ተመለስኩኝና ሌላ አስር ተቀነሰልኝ:: ከዚያም ስመለስ ሙሳ ተመለስና አስቀንስ አሉኝ። ተመለስኩና እንዲቀነስ ስማፀን አስር ሶላት እንድሰግድ ታዘዝኩኝ። ከዚያም ወደ ሙሳ ስመለስ አስቀንስ አለኝ። ተመለስኩና አስቀነስኩ:: በየቀኑ አምስት ሶላት አንድሰግድ ታዘዝኩ:: አሁንም በሙሳ በኩል ላልፍ 'በምን ታዘዝክ? አለኝ። በቀን ውስጥ የሚሰገዱ አምስት ሶላቶችን ታዘዝኡ አልኩት። ህዝቦችህ አምስት ሶላቶችን አይችሉም:: እኔ ወሏሂ ካንተ በፊት ሥዎችን ሞክሬያቸኋለሁ:: የእስራኤል ልጆችን ብርቱ ትግል ታግያቸኋለሁ:: ወደ ጌታህ ተመለስና ለህዝቦችህ እንዲያቀልላቸው ለምነው:: አለኝ:: ጌታዬን አስከማፍረው ድረስ ለመንኩት:: አሁን እንኳን ትዕዛዙን ወደድኩኝ፣ እጅም ሰጠኹ) አልኩኝና ስሄድ ተጣሪ ተጣራ:: ጥሪው እንዲህ ይል ነበር ግዴታዬን ደነገግኩኝ። ለባሮቼም አቀለልኩኝ::"

በሌላ ዘገባ እንዲህ የሚል እናገኛለን፡- “አላህ (ሱ.ወ) በእኔ ላይ ራእይ አወረደ:: በቀን እና በለሊት የሚሰገድ ሀምሳ ሶላት ግዴታ አደረገብኝ። ወደ ሙሳ (ዐ.ሰ) ስወርድ አላህ (ሱ.ወ) በህዝቦችህ ላይ ምን ግዴታ አደረገ?' በማለት ጠየቀኝ:: ሀምሳ ሶላት አልኩት:: 'ህዝቦችህ አይችሉም:: እኔ የእስራኤል ልጆችን ሞክሬያቸኋለሁ። ወደ ጌታህ ተመለስና እንዲቀንስልህ ለምነው:: አለኝ:: ወደ ጌታዬ ተመለስኩና ጌታዬ ሆይ ለህዝቦቼ አቅልልላቸው አልኩት:: አምስቱን አወረደልኝና ተመለስኩ:: በሙሳ በኩል ላልፍ አምኣት ተቀነሰልኝ አልኩት:: እርሱም ህዝቦችህ አይችሉም:: እኔ የእስራኤል ልጆችን ሞክሬያቸኋለሁ:: ወደ ጌታህ ተመለስና እንዲቀንስልህ ለምነው:: አለኝ:: በጌታዬና በሙሳ መሀል ከመመላለስ አልተወገድኩም:: ከዚያም 'መ አመድ ሆይ! እነዚህ አምስት ሶላቶች በቀንና በሌት የሚሰገዱ ናቸው:: ለእያንዳንዱ ሶላትም የአስር ምንዳ አለው። ይኸውም የሀምሳ ሶላት ምንዳ ማለት ነው:: መልካምን ሥራ ለመስራት አስቦ ያልሰራው ሰው አንድ ምንዳ ይፃፍለታል:: የሠራው እንደሆነ ደግሞ አስር ምንዳ ይፃፍለታል። ክፋትን ለመፈፀም አስቦ የተወው ሰው ምንም አይፃፍበትም:: የሠራው እንደሆነ ደግሞ አንድ ኃጢያት ይፃፍበታል:: ከዚያም ሙሳ (ዐ.ሰ) ጋር እስክደርስ ድረስ ወረድኩኝና ነገርኩት:: 'ወደ ጌታህ ተመለስና እንዲያቀልልህ ለምነው:: አለኝ:: መልእክተኛው ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እስከማፍረው ድረስ ወደ ጌታዬ ተመላልሻለሁ።' አሉ።"

12. ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከጉዞአቸው ሲመለሱ ለህዝቦቻቸው ስለመንገራቸው

ከዚያም መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ሲመለሱ በኢስራእ ጉዞአቸው የተከሰተውን ሁሉ እንዲነግሩ በመታዘዛቸው ወዲያው ለህዝቦቸቸው ነገሩ:: የሚዕራጁን ተአምር ግን አልገለፁትም ነበር። ህዝቦቹም ከእዚህ እዚያ ድረስ የወር መንገድ ነው:: አንተ እንዴት በአንድ ለሊት ደርሼ መጣሁ ተለናለህ? አሉ። ከሠዎቹ መሀል አንዳንዶቹ በይቱል መቅዲስን

ያውቁ ነበርና እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው "ቤተ-መቅደሱ ስንት በሮች አሉት?. አስደንጋጭ ጥያቄ ነበር። ምክንያቱም መልእክተኛው (ሲ.ዐ.ወ) ጉዞአቸውን ያደረጉት በለሊት ነው:: በዚያ ላይ ብዙ አስገራሚ ነገሮች የተከሰተበት ለሊት ነው። ተአምራቱ መንፈስን ከሌላ ነገር ጋር ይጠምዳል። ልብንም ይሞላል። እና በር መቁጠር ትዝ አይልም። ደግሞ የበሩን ቁጥር እዚያው የኖረ ሰው ራስ

ልብ ላይል ይችላል። ግን ከዚህ ከንቱ ጥያቄ ለመንጎድ ያሰፈሰፋ የክህደት ክንፎች መሰበር አለባቸው:: ስለዚህ መልእክተኛው

(ሰዐወ) አስፈላጊ ጥያቄ ባይሆንም መመለስ አለባቸው። የመልዕክቱና የትዕዛዙ ባለቤት አላህ (ሱ.ወ) በሮቹን እዚያው ቁጭ

ብለው ይመለከታቸው ዘንድ አሳያቸው እየተመለከቷቸውም ቆጠሯቸው። የቆጠሩትንም አንድ በአንድ ነገሯቸው : ካላመኑም ከዚህ ማብራሪያ በኋላ አይመኑ። ነገሩስ ማመን የፈለገ ሰው ጥያቄ አልጠየቀ!

ስለዚህ ወደ አቡበክር (ረ.ዐ) ሄዱ እምነቱን በሞገድ ማጠልሸት የሚችሉ መስሏቸው...

ንግግራቸው እራሱ ያዩትን እውነት በጭካኔ ለማረድ እንሚሞክሩ ያስታውቃል። ምን አሉ?..

ማደኛህ የኢስራ ጉዞ አደረኩኝ እያለ ይሞግታል!' አሉ። "ጓደኛህ የኢስራ ጉዞ አደረኩኝ አለ።° ቢሉና የማመን እና የከህደት ምርጫውን ለርሱ ቢተዉለት ምናለ?!...

“ጓደኛህ የኢስራ ጉዞ አደረኩኝ እያለ ይሞግታል!!' አሉ:: አቡብክር እምነቱ አእምሮ'ውን ያበሰለለት የአላህ ፍርሀት ልቡን ያሸበረቀለት ድንቅ ሰው ነበር። ሁሌም ቢሆኑ በማንኛውም ዘመን ከህደትን አንገት የሚያስደፋ ንግግር ተናገረ። “መሐመድ እንዲህ ካለ እውነቱን ነው!بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

እባካችሁን ሙስሊሞች የሁል ጊዜ መፈክራችን ይህ ይሁን- "መሐመድ ከተናገረ እውነቱን ነውዛም "መሐመድ ከተናገረ እውነቱን ነው!!!....

ጉድ ነው!

አቡብክር- በደስታ ሊበሩ ያኮበኮቡትን የከህደት ክንፎች ሰብረው ከእውነታ ለመሸሽ ያዘጋጁትን ሁሉ አመከነባቸው:: የተአምሩ ባለቤት እና የጉዳዩ አስረጅ የአላህ መልእክተኛ እስከሆነ ድረስ ሎጂክም ሆነ የአእምሮ መረጃዎች አይ,ቃወመ-ትም:: አቡበክር ታላቅ ንግግር ተናግረዋል፡ 'መሐመድ ከተናገረ እውነቱን ነው! ስለ ሰማይ ወሬ እየነገረኝ ያመንኩት ስለምድር ወራ ሲነግረኝ እንዴት አላምነውም!?"

ከኢስራ እና ሚዕራጅ ጉዞ የምንማረው

ኢስራእና ሚዕራጅ አንዳንድ ታላላቅ ጉዳዮችን ትኩረት እንድንሰጥ ቆም ብለን እንድናስተውል ያደርገናል:: ከነዚህ ፫፣፭:

የነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) ደረጃ ትልቅ መሆኑን እንረዳለን:: ከሌሎች ነብያት አንጻርም ከብራቸው የላቀ መሆኑን እንገነዘባለን። ይህ ክስተት የተከሰተው ረሱል(ሶ.ዐ.ወ) በህዝቦቻቸው ማስተባበል አዝነው ልባቸው በሀዘን በተሞላበት ጊዜ መሆኑ ተአምሩን ሌላ ትርጉም ይሰጠዋል:: የነብዩን(ሶ.ዐ.ወ) የተሰበረ ልብ መጠገን፥ ከትንሿ ሀገር መካ ውጭ ብዙ ሀገሮች በምድርና በሰማይ- የርሳቸው ወዲጆች መሆናቸውን ማስረዳት፤ የአላህ ባሮች ያሉትም ቢሆኑ ያለፉት- የቅርብ ወንድማሞች መሆናቸውን ማሳወቅና ትስስራቸው እንዲጠነክር ማድረግ.... የጉዞው አላማዎች ነበሩ::

በተጨማሪም የቁረይሾች የማስተባበል ሙከሪ በመልእክተኛው ተአምራዊ ምላሽና መለኮታዎ ማስረጃ ተገታ። ከንቱ ክርክራቸውም ተዘረረ:: ከዚህ ቀደም አይተውት የማያውቁትንና አሁንም ለታላቅ ተአምር በሄዱበት ጉዞ በእግረ መንገድ- ያዩትን የኢየሩሳሌምን ቤተ-መቅደስ የበር ቁጥር ነገሯቸው:: ጥያቂዎቻቸው በሙሉ ተመለሱ፣ ግን... አላመኑም።

የአቡበክር ሲድዲቅን (ረ.ዐ) ዕናት እናደንቃለን። “አስ-ሲድዲቅ” (እውነተኛው) የሚለውን ቅዕል ያገኙትም ይህን ከስተት እውነት በማለታቸው ነው:: ይህ አቋም አሁን ላለው ትውልድም ታላቅ ትምህርት አለው:: የአቡብከርን (ረ.ዐ) እና የሌሎቹንም የመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ምትኮች (ኸሊፋዎች) ደረጃ ከፍ ያለ መሆኑንም እንመለከታለን። በመርህ መፅናት ታላቅ ነገር ነው:: በተለይም በዚህ ዘመን ዕናት የታላቅ ሰዎች ምልክት ነው:: ምክንያቱም AILU ዘመን ለቅርቢቷ አለም ኢምንት ምንዳዎች ብለው መርሀቸውን የሚለውጡ ብዙዎች ናቸው:: እሴቶቻቸውንም ከንቱ በሆኑ ስሜቶች የሚሰርዙ በዝተዋል:: ሲድዲቅ ግን “እርሱ (ሙሐመድ) በዚህ ላይ እውነተኛ ነው:: የሠማይ ወሬ ሲነግረኝ ያመንኩት ስለምድር ሲነግረኝ እንዴት አላምነውም?" አሉ።

አንዳንድ ማቴሪያሊስቶች (ቁሳዊያን) እንደሚያስቡት (እንደሚጠረጥሩት) የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህማይ ጉዞ የእውንና የአካል ጉዞ እንጂ- የምናብ አሳቤ አይደለም:: ታላቅ ተአምር ያደረገውም ይኸው ነው:: በተለይም አሁን ባለንበት ጊዜ የሠው ልጅ ጠፈር ላይ

በዘመተበት ዘመን የሻውን ለማድረግ ዮሁን ቃል የሚቢቃው አላህ መልእክተኛውን ወደሰማይ ማምጠቁ አይሆንም የሚባል ነገር አይሆንም።

እውነተኝነት፣ ለእውነት ማበር፣ ከስሜት መራቆት፣ ከኩራት መራቅ... እንደሚያሻ ከኢስራእና ሚዕራጅ እንማራለን:: መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) የቁረይሾችን ጥያቄዎች ሁሉ መልሰዋል። የጉዞአቸውን እውነተኝነት በመረጃ አረጋግጠዋል። እንደውም ቁረይሾች የተአምራዊውን ጉዞ እውነተኝነት በማቴሪያሊስት እሳቤ መረመሩት። የቤ+- መቅደሱን በሮች ቁጥር ጠየቁ። እርሱንም መለሱላቸው። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን አላመኑም:: ሞገደኞች ሆኑ። ኩራት ወጠራቸው:: ስሜታቸው ነዳቸው:: ማስተባበል አሸነፋቸው:: እነዚህ መጥፎ አመሎች በየዘመኑ ብዙሀንን ከእውነት የጋረዱ ንብብር ግርዶዎች ናቸው:: ስለዚህ ሁሌም ቢሆን የሰው ልጅ ሊመከር የሚገባው እውነተኛ እና የእውነት አባሪ እንዲሆን ነው። ሁሌም መረጃን እንዲከተል። አእምሮውን ከስሜት እንዲያፀዳ እና አብዝቶ እንዲያስተውል ነው:: የሀቀኞች ደካማነትም ከእውነት እንዳያቅበው መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: እውነት በኃይል አይለካም:: የኋላ አሸናፊ እርሱ ቢሆንም....

የረጀብ ወር ታላላቅ ክስተቶች

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅና በጣም አዛኝ በሆነው። አሏህ የተመሰገነ ይሁን! ያ ሁሉን የፈጠረ! እዝነቱ ሰፊ! ቅጣቱ ብርቱ!

ከፍጥረታት ያሻውን የሚያልቅ ለሆነው አምላክ ከሥልጣኑ የሰፋ ሙገስ የተገባው

ነው።

የያዝነው ወር እንደ ሃጅራ አቆጣጠር ረጀብ ወር 1435 ነው:: የረጀብ ወር አላህ ቁርአን ውስጥ ካከበራቸው አራት ታላላቅ ወራት መሀል አንዱ ነው:: ረጀብ የሚለው ቃል ተከበረ፤ ተላቀ... የሚሉትን ትርጓሜዎች ይይዛል:: ወሩ በዚህ ስያሜ የተጠቀሰው በጃሂሊያ ጊዜ ሰዎች ያከብሩትና ያልቁት ስለነበር ነው:: ለርሱ ክብርም ጦርነት ይቆማል ፍልሚያ አይፈቀድም:: (አስ-ሲሓሕ ፊ አል-ሉጋ)

በዚህ ወር ውስጥ የተከሰቱ ታላላቅ የታሪክ አጋጣሚዎች አሉ። እነሱን በከፊሉ እነሆ-

1, ኢስራና ሚዕራጅ በዚህ ወር ሀያ ሰባተኛው ቀን ላይ የአላህ መልእክተኛ(ሶ.ዐ.ወ) ከመካ ከአጎታቸው ልጅ ቤት ወደ በይቱል መቅዲስ ፍልስጤም በሌሊት ተጉዘዋል ወደ ሰማይም አርገው ተመልሰዋል:: ጉዞው ተዓምራዊ ጉዞ ነበር። እዚያም ያለፉት ነብያት ሁሉ ተሰብስበውላቸው አማም ሆነው አሰግደዋቸዋል:: የርሳቸው የበላይነትና ክብርም ለፍጥረት ሁሉ ይፋ ሆነ።

2 የተቡክ ዘመቻ፡ ዘጠነኛው ዓመት እንደ ሃጅራ በረጀብ አሥረኛው ቀን የተከሰተ የረሱል(ሶ.ዐ.ወ) ታላቅ ዘመቻ ነው::

3 ነጃሺ (የሐበሻው ሙስሊም ንጉስ) ያረፉበት፡ ነዛሲ እስልምናውን እንደጠበቀ እንደ ሃጅራ ዘጠነኛው ዓመት በረጀብ ወር ውስጥ ሞተ። ነጃሺ(ረ.ዐ) በጣም መልካም ሰው ነበር። ታላቅ የአላህ ወዳጅም ነበር። በጃዕፈር ኢብኑ አቢጧሊብ(ረ.ዐ) መሪነት የመጀመሪያዎቹ የረሱል(ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ወደርሱ ተሰደዋል። ወደ እስልምናም ጠርተውት ከምርጥ ሙስሊሞች, ሆኗል:: የህልፈቱ ቀንም ረሱላችን(ሶ.ዐ.ወ) የጋኢብ(የሩቅ የጀናዛ) ሶላት ሰግደውበታል።

4,የየርሙክ ጦርነት ይህ ጦርነት በሙስሊሞችና በሮማውያን መሀል የተካሄደው ረጀብ 5 ከሂጅራ በኋላ 15ኛው ዓመት ነበር። ይህም እ.ኤ.አ. ኦገስት 12፤ 636ን ይገጥማል:: የየርሙክ ጦርነት ትልቅና ታሪካዊ ጦርነት ነበር። የጦርነቱ አሸናፊዎችም ሙስሊሞች ነበሩ። የጦርነቱ ውጤትም የሶሪያን ምድር ከማቅናት ጋሬጣ የነበረው የሮማውያን ከንድ መቆረጥ እና የሙስሊሞች ሀገርን የማቅናት ዘመቻ መጧጧፍ ነበር።

5, ዐባስ ኢብኑ ዐብዱል ሙጠሊብ ያረፉበት፡ እንደ ሃድራ ረጀብ 12፡ 32ኛው ዓመት ወይም እንደ ፈረንጆቹ ፌብሩዋሪ 161 652 ላይ የነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) አጎት ዓባስ ኢብነ ዐብዱል ሙጦሊብ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ዓባስ የዳንቷ ስምምነት (በይዐቱል ዐቀባህ) ላይ አነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) ጎን የቆመ የነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) አጎት ነበር:: መካ ከመከፈቷ በፊት ወደ መዲና መጥቷል:: ነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) ያከብሩት ነበር:: ከአምስት ምዕተ ዓመታት በላይ የሙስሊሙን ዓለም የገዛው የዕባሲያ ሥርው-መንግሥት በዘር ሐረግ ወደርሣቸው ይጠጋል። የታላቁ ሶሐባና የቁርአን ተርጓሚ ዓብዱሏህ ኢብኑ ዓባስ(ረ.ዐ) አባትም ናቸው።

6 ታላቁ ኽሊፋ ዑመር ኢብኑ ዓብዱል ዐዚዝ ያረፉበት ዑመር ኢብን ዕብዱል-ዐዚዝ በዚህ በያዝነው ወር ውስጥ 24ኛው ቀን ላይ እንደ ሃጅራ 101 ዓመት በሠላሳ ዘጠኝ ዓመታቸው አርፈዋል:: ይህ ዓመት እ.ኤ.አ ፌብሩዋሪ 6፡ 720 መሆኑ ነው:: እኚህ ታላቅ ኽሊፋ በዕውቀታቸው፣ በተቅዋቸው፤ ከዱንያ ደንታ ቢስ (ዛሃድ) በመሆናቸውና

በዚሁ ወር ውስጥ ሞተው ግብፅ ውስጥ ተቀበሩ። ይህ ቀን እ.ኤ.እ ጃንዋሪ 20፣ 820 ነው። እኚህ አማም በሀገራችን በስፋት የሚገኘው የሻፊዒያ መዝጋብ መሥራች መሆናቸው ይታወቃል። የቁረይሽ ዓሊም ምድርን በሙሉ በዒልም የሚሞላት አለ።"የሚለው የነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) ሐዲስ (ተርሚዚ ውስጥ የተዘገበው) እርሳቸውን ለማለት እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ። ፍልስጤም (ጋዛ) ውስጥ ተወልደዋል። ከዚያም ዒራቅ፣ መካ፣ መዲና እና ግብፅ ውስጥ ኖረዋል:: በመጨረሻም ግብፅ ውስጥ ተቀብረዋል።

6 አስ-ሲዩጢይ ውልደት ረጀብ 1 እንደ ሃጅራ 849 ዓመት ላይ ታላቁ ዐሊም ጀላሉዲን ዐብዱ-ራሕማን ቢን አዚ- በክር ጅላሉዲን አሱሲዩጢይ) ተወለዱ። እኚህ ዓለም ታላቅ የፊቾህ፤ የሐዲስ፣ የቋንቋ፣ የተፍሲር፣ የታሪክ እና ዐቂዳ (እምነት) ምሁር ናቸው:: ጀምዑል ጀዋሚዕ፡ ሑስኑል ሙሐደራ! "አድዱሩል መንሱሮ፣ "አል-አሽባህ

8 ኢብኑል ቀዩም ያረፉበት፤ ታላቁ ዓሊም ዐብዱ ሏህ መሐመድ ኢብኑ ቐዩም አል-ጀውዚያ ረጀብ 23 751 እንደ ሃጅራ ወይም እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 26 1350 ላይ አርፈዋል። እኚህ ታላቅ ዓሊም ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት (ሂጅራ) እንደ ዓይኖች የሚቆጠሩ ነበሩ። ሐዲስ፣ ፊቾህ' ታሪክ እና ተሰዉፍ ላይ በፃፏቸው መጽሐፍት

9 ሶላሑዲን አል-አየቢይ ቁድስን ያስመለሰበት ረጀብ 27 ከሂጅራ በኋላ 583 ላይ (እ.ኤ.እ ኦክቶብር 2፡ 1187) መስሊሞች በሰላሑዲን አል-አየቢይ መሪነት ወደ ተነጠቀችው የተከበረችው የቁድስ ከተማ ተመለሱ:: ቁድስ ከዚህ በፊት ለሰማንያ ስምንት ዓመታት ድረስ በመስቀለኞች በወረራ ተይዛ ነበር። ሶላሑዲን ቁድስን የተቆጣጠሩት ሂጢን የተባለችው ሥፍራ ላይ ታላቅ ድል ከነሳ በኋላ ነው:: ድል አድራጊው መሪ ወደ ቁድስ ሲገባ የመስቀል ጦረኞች በሙስሊሞች ላይ የፈፀሙትን እስካሁን ዓለምን የሚያሳዝን ፍፁም አስቃቂ ደም የማፍሰስ ድርጊት እነርሱ ላይ አልፈፀመም:: እንደውም ይቅር አላቸው:: በነፃነት እንዲኖሩም አደረገ:: ይህ ነው ኢስላማችን!!! የምንኮራባት ይቅርባይነታችን

ıo የቱርክ መንግሥት በአታቱርክ መሪነት ኣያ በተባለው ጥንታዊ መስጊድ ውስጥ ሶላት እንዳይሰገድ እና ውስጡ ያሉት መስገጃዎች፤ በዐረብኛ የተጻፉ ጥንታዊ የሎህ ጽሑፎችና ሚንበሩ ወጥቶ ለሶፊያ መዘክር እንዲሰጡ እና መስጊዱ ለቱሪስት መስህብነት እንዲውል አረመኔያዊ ውሳኔ አስተላልፏል:: ይህም የሆነው ረጀብ 16 1353 እንደ ሂጅራ አቆጣጠር (1925 GC)

የመጨረሻው ኢስላማዊ የኸሊፋ ሥርዓት ተጣለ ይህ ክስተት ረጀብ 27፣ 1342 እንደ ሂጅራ ወይም ማርች 1921 እ.ኤ.አ. ነበር። ሥርአቱ የኦቶማን የኸሊፋ ሥርዓት ነበር። የወደቀውም በሙስጦፋ አታቱርክ እጅ ነበር። ከዚያም አታቱርክ እራሱን የቱርክ ፕሬዝዳንት አድርጎ ሾመ:: የዑስማኒያን (ኦቶማን) ኸሊፋና ቤተሰቡን ከሀገር አባረረ ሙስሊሞቹ በኸሊፋው መመራት ቢሹም አታቱርክ መብታቸውን ነፈገ። በዚህም ምክንያት አኮብኩቦው የነበሩት የቅኝ ግዛት አውሮፓዊያን በሙስሊሞች መህል የነበረውን የመንፈሥ ትስስር መበታተን ቻሉ:: ለዓመታት ያለሙት ሕልምም ከብዙ ልፋት በኋላ ተሳካላቸው።

11, (የቱርክ መንግሥት (በአታቱርክ መሪነት)

ኣያ የተባለ ጥንታዊ መስጂድ ውስጥ እናዳይሰግዱ የቁርአን በዐረብኛ ቋንቋ ሳይሆን በቱርክ ቋንቋ እንዲነበብ አm o የሆነው ረጀብ 28፤ 1344 ወይም እንደ እውሮፓዊያን አቆጣጠር ፌበራሪ 21፣ 1925 ነበር።

12 የፓኩስታኑ ጀመዓህ ኢስላሚያ መስራች ዘቡል አዕላ አል መውዱዲ ረጀብ 3 1321 ወይም እ.ኤ.አ ሴፕቴምበር 25 1903 ተወለዱ:: ሰውየው ከዚህ ምዕተ ዓመት (እንደ ሂጅራ) ታላላቅ የዳዕዋ ሰዎች መህል የሚጠቀሱ ናቸው:: ቁርአንን ለመገንዘብ፣ የነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) ሲራ(የሕይወት ታሪክ)፣ ተፍሂመል ቁርኣን- ተፍሊር እና ሌሎች ጠቃሚ ድርሰቶች አሏቸው።

15 አሕመድ ዲዳት ያረፉበት ታላቁ የዘመናችን የዳዕዋ ሰው በሰማንያ ሰባት ዓመታቸው ነበር የሞቱት ቀኑም እንደ ሂጅራ ረጀብ 3፣ 1426 ሲሆን እ.አ.አ ሕንድ ውስጥ ነበር... ከዚያም ወደ ደቡብ አፍሪካ አቅንተዋል። ብዙዎችን ወደ እስልምና የመለሱባቸው የሃይማኖት ውይይቶችና ክርhe? ዲዳትን ያስታውሱናል። ዲዳት በአስልምናና ክርስትና መህል ምርጽ ቅዱስ የአምላክ ቃል ?

እና መሰል መጽሐፍትን ለሃይማኖቶች ውይይት ዓለም አበርክተዋል።

ኢስራእና ሚዕራጅ አስተምህሮትና ተግሳፅ

ሙስሊሞች በየዓመቱ አንድ ታላቅ ነቢያዊ ክስተት ያሳልፋሉ። አሏህ(ሱ.ወ) በተከበረዉ ቁርአን ዉስጥ ታሪካዊነቱን ዘግቧል። ከዛም አልፎ ክስተቱን የቁርአን ምዕራፍ መሰየሚያ አድርጎታል:: ያ ክስተት "የኢስራእና የሚዕራጅ' ሌሊት በመባል ይታወቃል:: ሀያ ሰባተኛው የረጀብ ሌሊት ላይ ነበር ይህ ተዓምራዊ ጉዞ የተደረገው::

“ኢስራእ” ማለት በየብስ የተደረገ የየብስ ጉዞ ነው:: አሏህ(ሱ ወ) ታላቁን ነቢይ(ሶ.ዐ.ወ) በአንድ ሌሊት ከመካ ወደ በይተል-መቐዲስ(ከመስጅደል-ሓረም ወደ መስጅደል-አቐሳ) እኑዲጓዙ ያስቻለበት ነዉ::

“ሚዕራጅ” ማለት ከምድር ወደ ሰማይ የተደረገ የሕዋ(ሰማያዊ) ጉዞ ነዉ:: የጉዞው መነሻ በይተል-መቐደስ ሆኖ ወደ

ሰማየ-ሰማያት የተደረገ እርግታ ነዉ:: ይህንን መዳረሻ የሰው ልጅ ኮቴ ረግጦት አያቅም:: "ሲደረተል-ሙንታሃ" ይሰኛል -የጉዞዉ መዳረሻ:: ምንነቱን አላህ(ሱ.ወ) ብቻ ነዉ የሚያዉቀዉ። እነኝህ ሁለት ጉዞዎች በነብዩ(ሶ.ዐ.ወ) ሕይወትና በመካ ዳዕዋቸው(ጥሪ) ላይ ወሳኝ እርከኖች ናቸዉ። ከመካ ቹረይሾች

ዓይነቱ የበዛ መከራን ካሳለፉ በኋላ ምናልባት “ሠቂይፍ” የተባሉ የጧኢፍ ጎሳዎች ዘንድ ተቀባይነትን የማግኘት ተስፋን ሰንቀው ወደ ጧኢፍ አመሩ:: ዳሩ ግን አስከፊ መልስ ነበር የጠበቃቸው:: ቂላቂሎቻቸዉን አሰባሰቡባቸዉ፤ ባሮቻቸዉን አዘዙባቸዉ በህፃናቶቻቻዉ ድንጋይ አስወረወሩባቸዉ:: የረሱል(ሶ.ዐ.ወ) እግር በደም ተጠመቀ:: አግልጋያቸዉ ዘይድ ብን ሓሪሣህ(ረ.ዐ) የሚወረወሩ ድንጋዮች እርሱ ላይ እንዲዘንቡ ይጥራል:: የረሱልን(ሶ.ዐ.ወ) ስቃይ ይቀንስ ዘንድ ይረባረባል። የራስ ቅሉ በርካታ ቦታ ላይ ተፈነከተ። በሰውነቱ ላይ የሚፈሰው ደም ጫማውንም አራስ፡

ረሱላችን(ሶ.ዐ.ወ) እግራቸዉ በደም ተጠምቆ ከጧኢፍ ወጡ። አሚዘንብባቸው የድንጋይ ናዳ የበለጠ ልባቸዉን ያደማው ይሰነዘሩባቸው የነበሩ የንቀትና የስድብ ቃላት ነበር። ለዚህም ነበር እንዲህ ብለዉ ዱዓእ ማድረጋቸዉ

اللهم إني أشكوا إليك ضعف قوتي وقلة حيلتي وهواني على الناس يا أرحم الراحمين أنت رب المستضعفين وأنت ربي إلى من تكلني إلى بعيد يتجهمني أم إلى عدو ملكته أمري إن لم يكن بك غضب علي فلا أبالي, ولكن عافيتك أسع لي، أعوذ

بنور وجهك الذي أشرقت به الظلمات وصلح عليه أمر الدنيا والآخرة أن ينزل بي غضبك أو يحل بي سخطك

"ጌታዬ ሆይ! የኃይሌን መድከም፣ የመላዬን ማነስና ሰዎች ዘንድ የደረሰብኝን ንቀት ለአንተ አቤት እላለሁ:: አንተ የአዛኞቹ ሁሉ አዛኝ አንተ የደካሞች ጌታ አንተ የኔ ጌታ ለማን ትተወኛለህ? ለሩቅ አጥቂ ትሰጠኝ ወይንም በጠላት እጅ ላይ ትጥለኝ? በኔ ላይ ተቆጥተህብኝ ካልሆነ በሚደርስብኝ ሁሉ ግድ የለኝም:: ነገር ግን እኔን ደህና ማድረገህ ለኔ የሰፋ ነዉ:: ጨለማዎችን

ባበራዉ በአንተ ብርሃን፤ የቅርቢቱም ይሁን የመጭውን ዓለም ያሳመረ በሆነዉ የአንተ ብርሃን

እጠበቃለሁ -ቁጣህ እንዳይወርድብኝ ወይም ጥላቻህ እንዳይሰፍርብኝ::"

ይህኔ አላህ(ሱ.ወ.) የተራራን መላኢካ ወደ ረሱላችን(ሶ.ዐ.ወ) ላአ።

"አንተ ሙሐመድ ሆይ! ሁለቱን ተራራዎች በነርሱ ላይ እንዳላትም ፍላጎትህ ከሆነ አደርገዋለሁ::" አላቸዉ።

አዛኙ ነቢይ(ሶ.ዐ.ወ) ይህንን ተቃወሙ:: እንዲህም አሉ:-

"(ከነዚህ ሰዎች ጀርባ) ከአብራካቸዉ እርሱን(አላህን) በብቸኝነት ያለማጋራት የሚያመልኩ ልጆችን አላህ(ሱ.ወ) እንደሚያወጣ ተስፋ አደርጋለሁ” አሉና ይህንን ዱዓ አስከተሉ:-

اللهم اهدي قومي فإنهم لا يعلمون...

“ጌታዬ ሆይ! የሚሠሩትን አያውቁምና ወደ ትክክለኛ ጎዳና ምራቸው።”

ከዚህ ክስተት በኋላ ነበር የኢስራእና ሚዕራት ጉዞ እዉን የሆነዉ :: የደረሰባቸውን መከራ ይረሱ: ስቃያቸዉን ያስታገሉ አቀባበል ከፍ ያለ ነዉ" እንደማለት ነዉ::

2ነኝ ሰዎች ሀገራቸዉን ሲከለክሉን ታለቁ አላህ(ሱ.ወ) ያስተናግድሀል: እንቢያዎች ይከተሉሃል- ኢማማቸዉም ትብናለህ::" የሚል መልዕክት ነበረዉ:: ይህ በርግጥም ለደረሰባቸዉ መከራ ማካካሻና አሏህ ዘንድ ያላቸዉን ልቅናም መጨመሪያ ነበር። በተጨማሪም ከሃጅራ በኋላ ላለው ወሳኝ እርአን እያዘጋጃቸዉ ነበር። ከሂጅራ በኋላ የዳዕዋ ሕይጠት ከባድ የትጥቅ ትግልንም ያካተተ ነበርና:: ዐረቦቹ በሙሉ በረሱላችን(ሶ.ወ)

ላይ አንድ ግንባር የሚፈጥሩበት ጊዜ ነው:: የተለያዩ ተቀናቃኝ ግንባሮች አንድነት ፈጥረው የረሱሉን ዳዕዋ ሊያጠፉ የሚነሱበት ወቅት ነዉ:: ዐረቢያ ደሴት ያለው ባዕድ አምላኪዎች በአንድ በኩል አሳት አምላኪ መጂሳዎች በሌላ በኩል፣ አላህ(ሱ.ወ) ያወረደዉን መጽሐፍ በመለወጥና ቃል ኪዳን በማፍረስ የሚታወቁት ሽፍጠኛ አይሁዶችም በአንድ ግንባር ተሰልፈዋል። ኢንጅልን የለወጡና ተዉሒድን ክጣዖታዊነት ጋር የቀላቀሉ ክርስቲያኖችም በሮማ ቤዛንታይን አዝማችነት አንድ ግንባር ናቸዉ::

ታዲያ ለዚህ ትልቅ ትግል ረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ.) መዘጋጀት ነበረባቸዉ። ዝግጅቱ እነኝህን ሁሉ ኃይላት በዕናት መጋፈጥ የሚያስችል መሆን ነበረበት:: ረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) እነኝህን ኃይላት በአናሳ ቁጥርና እዚህ ግባ በማይባል የሎጀስቲክ ዝግጅት መጋፈጥ አይቀርላቸዉም። እናም አላህ(ሱ.ወ) የምድርንም የሰማያትንም ተዓምራት ያሳያቸዉ ዘንድ ፈለገ።

سبحان الذي أسرى بعبده ليلا من المسجد الحرام إلى المسجد الأقصى الذي باركنا حوله لنريه من آياتِنَا إِنَّهُ هُوَ السَّمِيعُ البصير [١٧١]

'ያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኼደው (ጌታ) ጥራት ይገባው። ከተአምሮቶቻችን ልናሳየው (አስኼድነው)። እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚው ተመልካቺው ነው።" (አል-ኢስራእ (17)- 1)

በዚህ ፍጥረተ-ዓለም ውስጥ ያለን ተዓምር ይመለከቱ ዘንድ -ረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) በምድርም ብቻ ሳይገታ በሰማያትም ያለን አስደናቂ ተዓምራት ይመለከቱ ዘንድ! የነጅም ምዕራፍ ላይም ይህንን የሰማይ ተዓአምራትን አስመልክቶ አላህ(ሰ ወ) እንዲህ ይላል:-

ما زاغ البصر وما طَغَى لقد رأى من آياتِ رَبِّهِ الْكُبْرَى [١٧-٠٣-١٨]

ዓይኑ (ካየው) አልተዘነበለም:: ወሰንም አላለፈም:: ከጌታው ታ ላላቆቹን በእርግጥ አየ።። አን-ነጅም (53-17-18)

የረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) ልብ ይጠነክር፣ ጥንካሬያቸዉ ይታደስ፣ ሞራላቸዉ ይገንባና የክህደትን ማዕበል ከሁሉም አቅጣጫ መመከት ይችሉ ዘንድ ከታላላቅ ተዓምራቶች አሳያቸው::

የሶላት ግዴታ መሆን

ኢስራእና ሚዕራጅ ሰረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) ልቅና የተዘጋጀ ጉዞ ነበር። በመካም ሆነ በጧኢፍ ሕዝባቸዉ ያዴረሰባቸዉን ስቃይ ማስረሻና መንፈሳቸውን ማደሻም ነበር። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ አንድ ትልቅ ኃላፊነትም የተረከቡበት ጉዞ ነበር። ያ ኃላፊነትም ለወደፊት በራሳቸዉም ይሁን በተከታይ ሙስሊሞች ሕይወት ላይ ከባድ ተፅእኖ የሚኖረዉ ግዙፍ ኃላፊነት ነበር -ሶላት:: በዚህች ታላቅ ሌሊት አላህ(ሱ.ወ) ሶላትን ግዴታ አደረገ:: የአላህ ፍላጎቱ ነበር ወደ ሰዎች አምባሳደር የሆነዉን ታላቅ ሰዉ መጥራት:: ሙሐመድ(ሶ.ዐ.ወ):: በሌሊት ጉዞ ከተከበረው አአላህ(ሱ.ወ) ቤት መስጅደል ሓረም ወደ መስጅድል-አቐሷ ከዛም ሰማይ ሰማያትን አቋርጠው ሲደርተል-ሙንታሃን ረገጡ:: ይህ ጉዞ የኃላፊነቱን ክብደት ያሳያል። ሶላት ግዴታ ተደረገ። ሶላት በሙስሊም ግለሰብና ማኅበረሰብ ዘንድ ሊኖረዉ የሚገባዉን ትኩረትና ክብደት አመልካች ነበር:: ይህች ሰግደት(ሶላት) አንድ ባርያ ከጌታው ጋር የሚገናኝበት ቀጠሮ ነች::

ሶላት መጀመሪያ የተደነገገዉ ሀምሳ የሶላት ወቅቶች ሁኖ ነዉ:: በወንድማቸዉ ነቢዩላህ ሙሳ(ዐ.ሶ.ወሰላም) ምክር እየተመላለሱ ወደ አምስት ወቅት አስቀነሱ:: የአሏህ እዝነቱ ሰፊ ነውና በተግባር አምስት በአጅር ግን ሃምሳ ሶላት

2. ያባሪያውን በሚለው ሥፍራ መጥቀስ የተፈለገው ነብዩ ሙሐመድን(ሶ.ዐ.ወ) እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል። አሏህ እጅግ በጣም ስለሚያከብራቸው ሌሎች ነብያትን በስማቸው ሲጠራ ረሱላችንን(ሶ.ዐ.ወ) ግን በማዕረግ ስም መጥራቱ ምንያህል ቢልቁ ይሆን?

ያከል ሆኑ የተደነገጉት አምስት ጠቅት ሶላቶች:: በሌላ መልኩ አንድ ሰዉ ከአንድ ጉዞ መልስ ስጦታ(ሀድያ) ይዞ እንደሚመለሰዉ አዛኙ ነብይም(ሶ.ዐ.ወ) ከዚህ ተዓምራዊ ጉዞ መልስ ለዑመታቸዉ ሶላትን ሀድያ ይዘዉ መጡ። ሶላት ለሁሉም ሙስሊም ከረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) የተበረከተ ሀድያ እንደማለት ነዉ:: ይህች ታላቅ ሀድያ አንድ ሙስሊም የተላቀዉን ጌታውን ይገዛበታል። የመንፈስ እርካታንም ይጎናፀፍበታል:: ዉስጡን ያፀዳበታል:: የዱንያ ጭንቀቱን ያስወግድለታል በርግጥም ክርሷ ረፍትን ያገኛል:: ስክነት ዉሰጥ ይሆናል።

ሶላትን ስናስብ ምንግዜም መስጅደል-አቐሷን እናስታዉሳለን:: ያ የመጀመሪያዉ የሙስሊሞች ቸብላ ነው : ረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) ከተላኩ ጀምሮ ለሦስት ዓመታት ወደሱ ዙረዉ ሰግደዋል። ከዛም ፈታቸዉን ወደ ካዕባ ያዞሩ ዘንድ አላህ አዘዛቸው።

فَوَل وجهَكَ شَطْرَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ وحيث مَا كُنتُمْ فولُوا وُجُوهَكُمْ شَطْرَهُ [٢٠١٤٤]
“ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ)

አቅጣጫ አዙር:: የትም ስፍራ ብትኾኑ (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደርሱ አቅጣጫ አዙሩ።" አል በቀራ(2) -144)

መዲና ያሉ አይሁዶች በዚህ አምላካዊ ትዕዛዝ ላይ አሉባልታቸዉን እና ዉዝግቦችን እንሱ።

[٢ ١٤٢] سيقول السفهاء من الناس ما ولاهم عن قبلَتِهِمُ الَّتِي كَانُوا عَلَيْهَا አለዎቹ ቂሎቹ ከዚያች በርሷ ላይ ከነበሩባት ቂብላቸው ምን አዞራቸው?' ይላሉ-1" (አል-በቀራ(2)-142)

ከአሁን በፊት ይሰግዱት የነበረዉ ሶላት ውድቅ ሆነ" ሲሉም ወሬ ነዙ:: አላህም ለዚህ አለባልታቸዉ መልስ ሰጠ።

ومَا جَعَلْنَا القبلة التي كنت عليها إلا لنعلم من يتبع الرَّسُول ممن ينقلِبُ عَلَى عَقِبَيْهِ وَإِن كَانَتْ لكبيرة إلا عَلَى الَّذِينَ هدى الله وما كان الله لِيُضِيع إيمانكم إن الله بالنَّاسِ لَرَءُوفٌ رَّحِيمٌ [٢:١٤٣]

ያችንም በርሷ ላይ የነበርከባትን አቅጣጫ መልክተኛውን የሚከተለውን ስው ወደ ክህደት "

ከሚመለሰው ሰው ልናውቅ (ልንገልጽ) እንጅ ቂብላ አላደረግናትም:: እርሷም በነዚያ አላህ በመራቸው ሰዎች ላይ በስተቀር በእርግጥ ከባድ ናት:: አላህም እምነታችሁን (ስግደታችሁን) የሚያጠፋ አይደለም፤ አላህ ለሰዎች በጣም ርኅሩኅ አዛኝ ነውና::" (አል-በቀራ(2)1-143)

"ዕምነታችሁን ማለት ሶላታችሁን ማለት ነዉ:: ሶላትን ዕምነት ብሎ ገለጸ:: ምክንያቱም እምነት የሚገለሰበት ተግባር ነችና:: ሶላት ያችን የተባረከች ሌሊት ዘላለም እንድናስታዉስ ታደርገናለች::

የኢስራእና ሚዕራጅ ጉዞ አሰተምህሮቶች

ኢስራእና ሚዕራጅን ስናስብ ሁለት ዋና ዋና ቁም ነገሮች ላይ በጽኑ እናተኩራለን::

የመጀመሪያው የአቅሷ መስጂድ ነው:: አላህ(ሱ ወ) በመስጂደል-ሓረምና በመስጂደል-አቅሷ መካከል እንዴት ትስስር እንደፈጠረ እናስተዉላለን:: ረሱል(ሶ.ዐ.ወ) ከመካ ቀጥታ ወደ ሲደርተል-ሙንተሃ አላረጉም:: በሌሊት ጉዞ (ኢስራእ) ከመካ ወደ በይተል መቅዲስ ተጉዘዋል:: ይህ ትኩረት የሚሻ፤ አስተዉሎ የሚጠይቅ ነጥብ ነው:: ለምን ይሆን አላህ(ሱ.ወ) ይህንን ማድረጉ? ለምን ይሆን ሐረምን ከአቅሷ ማስተሳሰሩ? ይህ ከስተት አንድ ነገር ይጠቁመናል:: ረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) በዚህ በተቀደሰዉ በይተል መቅዲስ ማለፋቸዉ ድንገተኛ አልነበርም:: በይተል መቅዲስና ዙሪያዋ የተባረከች ምድር ነች። በበይተል-መቅዲስ ቆይታቸዉ ነብያትን ኢማም ሆነዉ አሰግደዋል። ይህ ከባድ መልእዕክትን ያዘለ ሁናቴ ነው:: ነብያቶችን በጠቅላላ ኢማም ሆነዉ ረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) የማስገዳቸው ትርጉም እንዲህ ነዉ።

የሰውን ልጅ የመምራት ኃላፊነት ወደ አዲሱ የረሱላችን (ሶዐወ) ዑማ ተሸጋግሯል። ነብይነትም ወደ መጨረሻው ነቢይ ተጠቅልሏል:: በርሱም በቅቷል:: የመጨረሻዉ ነቢይ ነውና ነቢይነቱ እንዳለፉት ነቢያት አይደለም:: እኒያ ነቢያት ለተወሰነ ሕዝብና ለተወሰነ ጊዜ ነበር የተላኩት የመጨረሻው ነቢይ ግን ለዓለማት ሁሉና ለዘለዓለሙ ነዉ የተላከሁ በዓለማት በሙሉ እዝነት ይሆን ዘንድ ነው ተልእኮው የመልእክቱ ሁሉን አቀፍ መሆንና ዘለዓለማዊ መሆን የግድ ነበር:: ይህ ነቢያትን ያስከተለ ሶላት እንድምታ ይህ ነበር:: መስኮት ነቢያት እን ኢብራሂም፣ ኢስለት፣ ሙሳ፣ 24፡ UR ነበሩባት ሀገር መዙ የአመራር ሽግግሩን ለማብሰር ነው:: ኢስላማዊው አመራር ወደ አዲሱ ዑማ ተሸጋግሯል። መልዕክቱ ወደ ዓለማቀፋዊነትና ዘለዓለማዊነት ሰፍቷል።

መስጅድ-አል ሐረምና መስጅድ-አል አቅሷ

በመስጅድ አል ሐረምና በመስጅድ አል አቅሷ መካከል የተፈጠረው ትስስር የሁለቱንም መስጂዶች ቅዱስነት በአጽንኦት ለማመልከት ነው:: እንዱ የኢስራእ መነሻ ሌላኛው መዳረሻ ነው:: በተጨማሪም አንዱ የሚዕራጅ መነሻ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከሚዕራጅ መመለሻ ሆኖ እናገናኘዋለን:: ይህ ክስተት አንድ ነገር ያስገነዝበናል - ዝተከበረው በይተል መቅዲስ ላይ ቸልተኛ መሆን በመስጅድ አል ሐረም ላይ ቸልተኛ ከመሆን ያልተናነሰ ነው:: " አላህ(ሱ.ወ) ሁለቱንም መስጅዶች በኢስራእ ማስተሳሰሩ በሙስሊሞች ልቦና ውስጥ የሁለቱንም መስጂዶች ክብር ከፍ ለማድረግ ነው:: መስጅድ አል አቅሷን በበረካ ገለጸው

[١٧] الَّذِي بَارَكْنَا حَوْلَهُ ዙሪያውን ወደ ባረክነው" (አል-ኢስራእ(17)-1)

ይህ መስጂድ በዚህ ክብር የተሰየመው ከመስጂደል ነበዊ (የመዲናው መስጊድ) በፊት ነው:: ምክንያቱም ኢስራእና ሚዕራጅ ከሃጅራ በፊት

ነውና። አላህ(ሱ.ወ) ሁለቱን የተቀደሱ መስጅዶች በዚህ ተዓምራዊ ክስተት ማስተሳሰሩ በሁለቱም በተከበሩ መስጅዶች ላይ ሙስሊሞች በሁለቱም መስጅዶች "ሐት ላይ ችላ እንዳይሉ ለማሳሰብ ነው:: የመስጂድ አል አቐሷን "ሐት ያጓደለ የመስጅድ አል ሐረምንም "ሐቅ ሊያጓድል የሚችል ሰው ነው:: መስጅድ አል አቐሷ የሙስሊሞች የመጀመሪያው ቂብላ ነበር። ሦስት ዓመታት በመካ እና አሥራ ስድስት ወራት በመዲና ወደ መስጅድ-አል አቐሷ አቅጣጫ ተሰግዷል። ያ የተቀደስ መስጅድ ለከብሩ ከሩቅ ሀገር ተጉዞ ሊዘየር (ሽዱ ሪኃል)የሚገባው መስጂድ እንደሆነ ኢስላም ያስተምራል። በርግጥም ከሩቅ ሀገር ለከብራቸውና ለቅዱስነታቸው ሊዘየሩ የሚገባቸው መስጅዶች መስጅድ-አል አቐሷን ጨምሮ መስጅድ አል ተረምና መስጅድ አነ-በዊይ ናቸው።

አላህ(ሱ.ወ) የመስጅድ አል አቐሷን ጉዳይ ዘለዓለማዊና በየዓመቱ ከረጀብ መጨረሻ ቀናት ጋር ተያይዞ ከሚታወሰው ኢስራእና ሚዕራጅ ጋር አስተሳስሮታል። የጉዳዩን ክብደት እንረዳ፤ የቦታውን ቅዱስነት እንገነዘብ ዘንድ ነው:: እናም በሙስሊሞች ልብ ውስጥ ለዘለዓለም ይኖራል::

ሶላት

ሶላት የተደነገገችው በተዓምረኛዋ የኢስራእና ሚዕራጅ ሌሊት መሆኑ የሶላትን ክብደት ያስተምረናል:: በዘመናችን ያሉ መንግሥታት ከሌላ መንግሥታት ጋር ከበድ ያለ ጉዳይ ሲኖራቸው ለአምባሳደሮቻቸው መልዕክት ከመላክ ይልቅ አምባሳደሮቻቸውን በአካል ይጠራሉ:: ይህ የጉዳዩን ከባድነት ለማስገንዘብ የሚደረግ ነው:: ከፍ ያለ ምሳሌ ለአላህ(ሱ.ወ) የተገባው ነው:: ረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) ወደ ሰው ልጆች የተላኩ የአላህ(ሱ.ወ) አምባሳደር ናቸው። አላህ(ሱ.ወ) አምባሰደሩን በሌሊት ወደ በይት አል መቐዲስ አስጉዞ ወደ ሰማየ ሰማያት በማሳረግ ሲድረተል ሙንተሀ አደረሳቸው:: እዚያ የተላቀ ስፍራ ላይ አምስቱ ወቅት ሶላቶች ተደነገጉ።

ሁሉም ድንጋጌዎች መሬት ላይ ነው የተደነገጉት:: ሶላት ብቻ ሰማይ ላይ ነው የተደነገገው:: ይህ የሶላትን ቦታ ከፍ ያደረገ ክስተት ነው። ሶላት በረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) “ሚዕራጅ” (አርገት) ጊዜ መደንገጓ ከዚህ ተዓምራዊ ጉዞ እስከ ምጽዓት ቀን ቀሪ የሆነ ፋና ይታያል። ረሱሉ(ሶ.ዐ.ወ) በአካል ያደረጉትን እርገት እያንዳንዱ ሙስሊም በመንፈሳዊ እርገት ይገልጸዋል። ያ መንፈሣዊ ጉዞ ሶላት ነው:: ሶላት ኢማናዊ እርገት ነው። እያንዳንዱ ሙእሚን በሶላት አማካኝነት መንፈሣዊ እርገት ይፈጽማል:: ከፈጣሪው ጋር ይገናኛል። ለዚህም ነው አላህ(ሱ.ወ) በሐዲስ-አልቁድስ ይህንኑ እውነታ

ያስቀመጠልን

قسمت الصلاة بيني و بين عبدي قسمين ولعبدي ما سأل فإذا قال عبدي الحمد لله رب العالمين, قال الله

تعالى: حمدني عبدي، فإذا قال: الرحمن الرحيم, قال تعالى: أثنى علي عبدي، فإذا قال: ماللك يوم الدين, قال

الله تعالى مجدني عبدي، فإذا قال: إياك نعبد و إياك نستعين قال الله تعالى: هذا بيني وبين عبدي، ولعبدي ماسأل، فإذا قال: اهدنا الصراط المستقيم إلى آخر الفاتحة قال الله تعالى: هذا لعبدي، ولعبدي ما سأل.

*ሶላትን በእኔና በባሪያዬ መካከል ከሁለት ከፍያታለሁ። ባሪያዬ የለመነውን ያገኛል:: ባሪያው: አልሐምዱ ሊላሂ ረቢልዓለሚን' ሲል፣ አላህ(ሱ.ወ) ባሪያዬ አመሰገነኝ ይላል። 'አር-ረሕማኒ አር-

ረሂም' ሲል፣ አላህ(ሱ.ወ) ባሪያዬ አወደሰኝ ይለዋል:: ማሊኪየው-ሚዲን ሲል፣ አላህ(ሱ.ወ) ባሪያዬ

አላቀኝ ይላል። 'እያከነዕቡዱ ወኢያከነስተዒን' ሲል፣ አላህ(ሱ.ወ) 'ይህ በእና በባሪያዬ መካከል ያለ ጉዳይ ነው:: ባሪያዬ የለመነውን ያገኛል' ይላል:: 'ኢህዲነሲራጠል ሙስተቂም' እስከመጨረሻው የፋቲሐ ምዕራፍ ሲያነብ፣ አላህ(ሱ.ወ) 'ይህ የባሪያዬ ጉዳይ ነው:: ባሪያዬ የለመነውን ሁሉ ያገኛል::' ይለዋል።"

ይህን ያክል ክብር የተቸረው ሶላት ከመስጅድ-አል አቐሷ ጋር ያለውን ትስስርም ማስተዋል የግድ ይላል:: ሶላት ከተደነገገ በኋላ የመጀመሪያው ቂብላ መስጅድ-አል አቐሷ ነውና።

እናም ከኢስራእና ሚዕራጅ ሁለት ዋና ዋና አስተምህሮቶችን እንወስዳለን። መስጅድ-አል አቐሷን በሚመለከት የሙስሊሙ ዑማ ኃላፊነት አንዱ ሲሆን፣ የሶላትን ክብርና ከመስጅድ-አል አቐሷ ጋር ያለውን ትስስር በውሉ መገንዘብና አቅሷን ሁሌም ከልባችን ማስተዋስ ሌላኛው ነው::

ጁመዓ ሰኔ 7/2004 ዓመተ-ልደት